# የቤት ግንባታና ማስረከብ ውል ማሻሻያ፣

ይህ የቤት ግንባታና ማስረከብ ውል ማሻሻያ በካንትሪ ክለብ ዴቨሎፐርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አድራሻ አዲስ አበባ ክፍለ ከተማ ቦሌ ቀበሌ 03/05 የቤት ቁጥር 2219 ስልክ ቁጥር 0116-18-71-01/0116-62-25-82 ከዚህ በኋላ ‹‹ቤት ሠሪ›› እየተባለ በሚጠራው..

እና

በ____________________አድራሻ ሀገር ______ከተማ ______ወረዳ _______ ቀበሌ______የቤት ቁጥር______የቤት ስልክ ቁጥር ______________ ሞባይል _____________የቢሮ ____________ የጎረቤት___________ፖ.ሣ.ቁ.____________ኢ.ሜይል____________ፋክስ____________ወይም የተለየ፣__________________________ ከዚህ በኋላ ‹‹ቤት አሠሪ›› እየተባሉ በሚጠሩት መካከል ዛሬ _____________ቀን____ዓ.ም ተፈርሟል፡፡

## አንቀጽ 1

## የማሻሻያ ውሉ ዓላማ፣

የዚህ ውል ዓላማ ባጋጠመው ከአቅም በላይ የሆነ የግንባታ ግብአትና መሣሪዎች ዕጥረትና ዋጋ መጨመር ምክንያት በቦታ ቁጥር (Plot No) ________በ __________ ቀን ______ዓ.ም በቤት ሠሪ እና አሠሪ መካከል በተደረገው የቤት ግንባታ ውል ላይ የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ ነው፡፡

## አንቀጽ 2

## የቤት አሠሪ መብትና ግዴታ፡፡

ቤት አሠሪ፡-

2.1 _____________ቀን______ዓ.ም በተፈረመው የቤት ግንባታና ማስረከብ ውል አንቀጽ 3.1 ሥር የተቀመጠው የቤት ዋጋ እንደተጠበቀ ሆኖ ዛሬ________ቀን_____ዓ.ም ብር _______ (__________________________) ተጨማሪ ክፍያ ፈጽሟል፡፡

2.2. በቀድሞው ውል የተቀመጠውን የቤት ዋጋ በውሉ አንቀጽ 7 መሠረት ከፍሎ ከላይ በተጠቀሰው የቦታ ቁጥር ላይ በመገንባት ላይ ያለውን ቤት _______ ቀን 200__ዓ.ም ግንባታው ተጠናቆ ለመረከብ ተስማምቷል፡፡

2.3 ‹‹ቤት ሠሪ›› በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቤቱን ጨርሶ ካላስረከበ የማስረከቢያው ጊዜ ተራዝሞ ለተራዘመበት ጊዜ 0.1% ፐርሰንት በየቀኑ 10% እስኪደርስ ድረስ ኪሣራ ለመቀበል ተስማምቷል፡፡

2.4 በመጀመሪያው ውል ላይ የተቀመጠውን የቤት ዋጋ በውሉ አንቀጽ 7 ሥር በተቀመጠው የአከፋፈል ሁኔታ ሊፈጽም ተስማምቷል፡፡

## አንቀጽ 3
## የቤት ሠሪ ግዴታ፡፡

**ቤት ሠሪ፡-**

3.1 ከዚህ በላይ ባለው አንቀጽ 2.2 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የቤቱን ግንባታ ጨርሶ ለማስረከብ ተስማምቷል፡፡

3.2 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የቤቱን ግንባታ ጨርሶ ካላስረከበ በዚህ ውል አንቀጽ 2.3 የተቀመጠውን ቅጣት ለመክፈል እና ቤቱን አጠናቅቆ ለማስረከብ ተስማምቷል፡፡

3.3 በቀድሞው ውል አንቀጽ 3 ሥር የተቀመጠውን የቤት ዋጋ በውሉ መሠረት እና በዚህ ውል አንቀጽ 2.1 ሥር የተጠቀሰውን ተጨማሪ ክፍያ በታህሣስ 2003 ዓ.ም ወር ውስጥ በቤት አሠሪ ከተከፈለ ሌላ የዋጋ ጭማሪ ላያደርግ ተስማምቷል፡፡

## አንቀጽ 4
## ይህ የማሻሻያ ዉል የመሠረታዊ ውሉ አካል ስለመሆኑ፣

ይህ የማሻሻያ ውል ከዚህ በፊት በ___________________ቀን _______ዓ.ም የተፈረመው መሠረታዊ ውል አካል እንዲሆን ቤት ሠሪ እና ቤት አሠሪ ተስማምተዋል፡፡

## አንቀጽ 5
## ተፈፃሚነት፣

5.1 ይህ ውል የሚፈረመው የሚደረገው ክፍያ በአንድ ጊዜም ሆነ በተለያየ ጊዜ ጠቅላላው እንደተከፈለ ይሆናል፡፡

5.2 ይህ ውል ከዛሬ ____________ቀን ______ ዓ.ም ጀምሮ በተዋዋዮች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 6

ቤት ሠሪ እና አሠሪ ይህን ውል ወደንና ፈቅደን በዛሬው ዕለት ተፈራርመናል፡፡

| ስለ ቤት ሠሪ፣ | ስለ ቤት አሠሪ፣ |
|---|---|
| ስም፣ ____________________ | ስም፣ ____________________ |
| ፊርማ፣ __________ | ፊርማ፣ __________ |

እኛም እማኞች ቤት ሠሪና ቤት አሠሪ ይህንን ውል ሲዋዋሉና ሲፈራረሙ ያየንና ውሉንም ያነበብን መሆኑን በፊርማችን እናረጋግጣለን፡፡

| | የእማኞች ስም፣ | የእማኞች ፊርማ፣ |
|---|---|---|
| 1. | ____________________ | ___________________ |
| 2. | ____________________ | ___________________ |
| 3. | ____________________ | ___________________ |